የሰ/መ/ቁ. 38289

ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ነጂሃ ድዋሌ ዋይስ - አልቀረበችም፡፡

**ተጠሪ፡-** አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ - ነ/ፈጅ ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03497 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው፡፡ በመዝገቡ እንደተመለከተው ጉዳዩ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበችውን የገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ልትመሠርት የቻለችው ድሬዳዋ በሚገኘው ቅርንጫፉ በኩል ተገቢውን የአገልግሎት ኮሚሽን በመክፈል አዲስ አበባ በሚገኘው ሲዳሞ ተራ በሚባለው ቅርንጫፉ አቶ ሽሪፍ ከዲር ለተባለ ሰው እንዲሰጥ የላከችውን ብር 45,000 (አርባ አምስት ሺህ) ለማይመለከተው ሰው ከፍያለሁ በማለት አደራውን አልተወጣም በማለት ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ገንዘቡ አመልካች በገለጸችው ሁኔታ መላኩንና የደረሰው መሆኑን ሳይክድ ነገር ግን ገንዘቡ የተላከልኝ ሰው እኔ ነኝ በማለት መታወቂያ ይዞ ለመጣ ሰው መክፈሉን በመግለጽ ከክሱ በነፃ ይሰናበት ዘንድ እንዲወስንለት ጠይቆአል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም በዚህ መልክ የቀረበውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ ክሱን ውድቅ በማድረግ ተጠሪን በነፃ አሰናብቶአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበል ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጭበርብሮ ገንዘቡን ለማይገባው ሰው የከፈለው ተጠሪ መሆኑ እየታወቀ ገንዘቡን ለአመልካች ለመተካት አይገደድም በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ተገቢውን ኮሚሽን በመክፈል ገንዘቡን ለባንኩ አስረክባለች፡፡ ገንዘቡን ለባንኩ የሰጠችውም ለተላከለት ሰው እንዲያደርስላት ነው፡፡ በእርግጥም ባንኩ የተሰጠው አደራ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ማድረስ እንደመሆኑ የማድረስ ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ባንኩ /ተጠሪ/ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው አላደረሰም፡፡ ይልቁንም ለማይመለከተው /ላልተላከለት/ ሰው መክፈሉ ተረጋግጦአል፡፡ በተጠሪ ክርክር እንደተገለጸው ገንዘቡን የከፈለው የተላከልኝ ሰው እኔ ነኝ የሚል መታወቂያ ደብተር የያዘ ሰው ስለቀረበ ነው፡፡ ይህ ሰው ግን በእርግጥም አመልካች ገንዘብ የላከችለት ሰው አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ የተጭበረበረው ተጠሪ /ባንኩ/ እንጂ አመልካች አይደለችም፡፡ አጭበርባሪውን ሰው ከሶ ገንዘቡን ማስመለስ የሚችለውም ተጠሪ እንጂ አመልካች ልትሆን አትችልም፡፡ ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው በአመልካች እና አጭበርብሮ ገንዘቡን ከተጠሪው ባንክ በወሰደው ሰው መካከል ምንም አይነት ግንኙነት የለም፡፡ ተጠሪ ስለተጭበረበረ አመልካችም እንደተጭበረበረች ይቆጠራል ወደሚለው መደምደሚያ የሚደርስ ሁኔታ የለም፡፡ በዚህ መዝገብ

የተያዘው አከራካሪ ሆኖ የተነሣው ነጥብ ባንክ ሂሣብ /ገንዘብ/ ባላቸው ሰዎች ስም ሌሎች ሰዎች አጭበርብረው ገንዘብ ከሚያወጡበት ሁኔታ ተለይቶ የሚታይ ነው፡፡ ባንክ ገንዘብ ያስቀመጡትን ሰዎች ሰነዶች እና ፊርማ አጭበርብሮ በማግኘት ገንዘብ የሚወስዱ ሰዎች በባለሂሣቦቹም ሆነ በባንኩ ሊጠየቁ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ባንኩን አጭበርብሮ ገንዘብ የወሰደውን ሰው በመጠየቅ ገንዘቡን የምታስመልስበት አግባብ የለም፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ተጠሪ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ለመስጠት ከአመልካች ሲቀበል የአደራውን ሃላፊነት ወስዶአል፡፡ አደራ ተቀባይ የሆነው ወገን በአደራ ያስቀመጠውን /የተቀበለውን/ ዕቃ መመለስ ያለበት ለአደራ ሰጪው ወይም አደራ ሰጪው ይቀበልልኝ ብሎ ላመለከተው ሰው እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2792/1/ በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪ ከእነዚህ ግዴታዎቹ አንዱንም አልተወጣም፡፡ ስለዚህም ገንዘቡን ለአመልካች አልከፍልም የሚልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከዚህ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21113 ኀዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03497 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለአመልካች ይመልስ ብለናል፡፡ በሥር ፍ/ቤቶች እና በዚህ ሰበር ችሎት አመልካች የከፈለችው የዳኝነት ገንዘብም ተጠሪ ይተካላት ብለናል፡፡
3. ሌሎች ወጪና ኪሣራ በተመለከተ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ